# አገሬ የሚል ዞሮ-ዞሮ ለመላው ነው።

## ግርማዊ ጃንሆይ የማኅበሩን ሕንጻ ሲጐበኙ ያደረጉት ንግግር።



ማኅበራዊ አንድነት የሚባለው አዳምና ሔዋን ሁለት ቢሆኑም ከነርሱ ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ነው ለማለት ይቻላል። ከዚያም ቀጥሎ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በመሔድ መጠን ማኅበራዊ አንድነት እየተስፋፋ ለመሔድ በቅቷል።

አገሬ የሚል ሰው ሁሉ በማኅበራዊ አንድነት ውስጥ ያለ በመሆኑ ማንኛውም ማኅበር በየትም ቢቋቋም አገልግሎቱ ዞሮ ዞሮ ለመላው ነው። እንዲሁም አገሬ ብሎ በሚጠራው በኢትዮጵያ ስም ሁሉም ማኅበርተኛ ነው ማለት ነው።

አሁን ማኅበራችሁን ጽኑ መሠረት ለማስያዝ ቦታ ገዝታችሁ ይህንን ቤት ለመሥራት በመቻላችሁ በተለይም ደግሞ ከራሳችሁ አዋጥታችሁ በትምህርት ለሚረዱት በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አሳብ ለሚለዋወጡት ይህንን አዳራሽ መመሥረታችሁ የሚያስደስት ነው። ከዚህም በቀር ማንኛውም ሰው ሊገለገልበት የሚችል የመጻሕፍት ቤት ማቋቋማችሁ እውነተኛ የማኅበርተኛነት ሥራ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ይህንን በጐ ዓላማ ስለመረጣችሁና ይህንንም ማኅበር ስላቋቋማችሁ የወደፊት ሥራችሁን ሊያቃናው ይችላል። እውነተኛውም የኢትዮጵያ አንድነት የሚባለው እንደዚሁ ማንንም ሳይለያይ ሲሠራና በኅብረት ልዩ ልዩ ጠቃሚ ድርጅቶችን ሲያቋቁም ነው። በእዚህ ንግድ ት/ቤት የተማራችሁ ሁሉ ይህንን ፍሬ ለማስገኘት መብቃታችሁ ልክ የእናንተኑ ያህል ወይንም በይበልጥ ደስ የሚያሳኘን ነገር ነው።

ይህ ለኢትዮጵያ አንድነታዊ ኑሮ ጽናትና ኃይል ሊሆነው ይችላል። ሰው ባለው ዘመኑ ላይ ለሰው ከመትረፍ የተሻለ አንድም ነገር የለም። አለበለዚያ ብቻውን ያልተፈጠረ ሰው ለሌላው ለመትረፍ ካልቻለ ለራሱም ሰይሆን ለሌላውም ሳይረዳ የሚቀር በመሆኑ እንደሌለ የሚያስቆጥረው ነው።

የጀመራችሁት በጐ አሳብና ዓላማ ለሌላው ምሳሌ መሆን ስላለበት በአዲስ አበባ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም። እንደዚሁ በየሥፍራው የፍቅር ማኅበር እያቋቋማችሁ የመረዳዳትንና የመተባበርን ዓላማ ብታስፋፉ ለአገራችሁ ከፍ ያለ አገልግሎት ለማበርከት ትችላላችሁ። ሌላውም ቢሆን ይህንን ምሳሌ ተከትሎ የመረዳጃ ማኅበር ቢያቋቁም ራሱን ብቻ ሳይሆን አገሩንም ጭምር እንደረዳ የሚያስቆጥረው ነው። ስለዚህ የተቻላችሁን ያህል በምትነጋገሩበትና በምትሠሩበት ጊዜ ሁሉ ለአገር ጥቅም የሠራነው ምንድነው ብላችሁ ራሳችሁን በትጠይቁ የጣላችሁት መሠረት በጠቅላላ ብቻ ሳይሆን በዝርዝርም ለእያንዳንዱ ግለሰብ የሚጠቅም መሆኑን ትረዳላችሁ።

እንደምታውቁት በመጻሕፍት የተባለው ንቃ አትተኛ ነው። በመጻሕፍት የተነገረውን ቃል በመከተል የሚነቃ ሰው የአገሩን ሰው ሁሉ እንደወንድሙ መመልከትና መርዳት ከዚያም ተርፎ ላገር የሚጠቅመውን ለመሥራት ይችላል። ደግሞ ራስክን አትውደድ ሲል እንዳልተፈጠርክ ሁን ማለት አይደለም።

ማንኛውም ሰው ራሱን መጠበቅና ቤተሰቡን በሚገባ ማስተዳደር አለበት። ከዚህም በተረፈ ግን ከልዩ ልዩ መጥፎ ሥራዎች እየተጠበቀና እየታረመ ራሱን በቁም ነገር ላይ ማዋል ይገባል።

ስለዚህ ይህን የጀመራችሁትን እንድታጸኑና ወደፊት እንድትገፉበት ያስፈልጋል።

አሁን በተናገርከው ውስጥ ይህን ያህሉን ከፍለን ይህን ያህሉ ቀርቶናል። ይህን ያህል አውጥተን እንደዚህ ያለ ሥርተናል በማለት ገልጠሃል። የተሠራው ሥራ በጣም ዋጋ ያለው ነገር ነው። ለእናንተም ለራሳችሁ ቢሆን የፈጸማችሁት ሥራ ደስ የሚያሰኛችሁ ነው።

እኛም ዛሬ ልንጐበኛችሁ የፈቀድነው ምንጊዜም ቢሆን በመንፈስ በማኅበራችሁ ውስጥ የእኛው ናችሁ ብለን የምናያችሁ ስለሆነ ነው። እናንተም ይህንን እንደዚሁ ሳትገነዘቡት ትቀራላችሁ ብለን አንገምትም።

አሁን ልንረዳችሁ የምትፈልጉት በንግግራችሁ ውስጥ የተጠቀሰው እንደሆነ ቀላል ነው። ሌላም ነገር የምንረዳችሁ እንዳለ ብትነግሩን እንደኛው ስለምንቆጥራችሁ ልንረዳችሁ እንፈቅዳለን።

ይህንን የመሰለውን በጐ መንፈስ ያረፈበት ተግባር ለሌላው ያካፈላችሁ እንደሆነ የበለጠ ትላቅ ነገር ነውና የተናገራችሁት ቃል እንደገና መልሶ ወቃሻችሁ እንዳይሆን በርትታችሁ ሥሩ።

የሰው ልጅ ይህንን ሁሉ ለማድረግ የሚችለው አገልጋይነቱንና ልቡን ከእግዚአብሔር ሳይለይ እሱ ያደርግልናል እሱ ይሠራልናል በማለት ሲሠራ ነውና ለዚሁ እግዚአብሔር ይርዳችሁ።

ኅዳር ፲፱ ቀን፲፱፻፷፩ ዓ.ም